በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ ከ4 — 6 ሰዓት ለሚካሔዳው የልጆች መርሐ ግብር
በምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል ላሉ ተማሪዎች የተዘጋጀ ሳምንታዊ ትምህርት

# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 22 ኛ ሳምንት

## እግዚአብሔር ይስጥልኝ - አመሰግናለሁ በሉ

**ዓላማ**

- ዘወትር እግዚአብሔርን አመሰግንሃለሁ እንዲሉ ማስተማር::
- በሰዎች ሁሉ ፊት ትሁታን እንዲሆኑና አመሰግናለሁ ማለት እንደሚገባቸው ማስገንዘብ::

**ጥቅስ**

- «እግዚአብሔርን እያመሰገነ እያከበረም ተመለሰ::» ሉቃስ 17 : 16

**ምንባብ**

- ሉቃስ 17 : 11-19

**መግቢያ**

- ያለፈው ጊዜ ትምህርትና ጥቅስ ያስታውሱአቸው::
- ሕፃናቱን መቼ አመሰግናለሁ እንደሚሉና እግዚአብሔር ይስጥልን ብለው የሚመልሱትም
- መቼ እንደሆነ ይጠይቋቸው::
- አመሰግናለሁ የምንለው ማንን ነው? ብለው ይጠይቋቸው::

**የትምህርቱ መግለጫ**

- የዛሬው ትምህርት አመሰግናለሁ ስላለ እግዚአብሔር ስለተደሰተበት ሰው ነው::
- አንድ ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መንደር ገባ::
- በዚያም መንደር የሰውነታቸው ቆዳ በጣም የተጎዳ አስር ሰዎችን አገኘ::
- ማንኛውንም ሰው እንዳይነኩ ተከልክለው ነበር::
- አስሩም ሰዎች ጌታችን ሲያዩት በሩቅ ሆነው ጌታ ሆይ ማረን ብለው ጮሁ::
- ጌታችንም ወደ ቤተመቅደስ ሄደው ራሳቸውን ለካህናት እንዲያሳዩ ነገራቸው::
- ካህናት ዛሬ በቤተክርስቲያናችን እንደምናያቸው አባቶች ናቸው::
- ወደ ቤተመቅደስም ሄደው ደህና ሆኑ:: ተፈወሱ::
- የሰውነታቸው ቆዳ ዳነ እንደጤናማ ሰውም ሆኑ::
- ከአስሩ ሰዎች ውስጥ አንዱ ብቻ ጌታ ሆይ ስላዳንከኝ አመሰግናለሁ ለማለት ወደ ጌታችን ተመልሶ መጣ:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ሰው ደስ አለው::
- ጌታችን ሌሎቹ የዳኑት ዘጠኙ ሰዎች ወዴት ቀሩ? ብሎ ተገረመ::
- ዘጠኙም እናመሰግናለን ለማለት ተመልሰው አልመጡም ነበር::
- ሊያመሰግን የመጣውን አንዱን ሰው ግን ባረከውና ከዚህ በኋላ ከቤተሰብህም ጋር በሰላም ኑር ብሎ ወደ ቤተሰቦቹ ሸኘው::

**ማጠቃለያ**

- መልካም ነገር ሲሰጣቸው አመሰግንሃለሁ የሚሉ ሕፃናትን እግዚአብሔር ይወድዳል::
- ሌሎች ሰዎች ስላደረጉላቸውም መልካም ነገር እናመሰግናለን የሚሉ ሕፃናትንም ይወድዳቸዋል::

**ተግባር**

- የአስሩን ሰዎች ሥዕል አምጥተው ሕጻናቱ እንዲቆጥሩአቸው ያደርጓቸው::
- ከአስሩ ተመልሶ በመምጣት ያመሰገነውን ሰው ሥዕል ያሳዩአቸው::
- አስር ስቲክሮች አዘጋጅተው በነጭ ወረቀት ላይ እንዲለጥፉ ያድርጓቸው::
- ሲጸልዩ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግናለሁ እንዲሉና ማንኛውም በጎ ያደረገላቸውን ሰው እግዚአብሔር ይስጥልን እናመሰግናለን እንዲሉ ያሳስቡአቸው::

**ይቆየን::**

አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ     የካቲት ፳፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.